# የ STREAM™ የጥገና እና የማስተካከል ሂደት

## ኦፕሬተር

| Led ቀለም አመልካች | መንስኤ | የኦፕሬተር የማስተካከያ እርምጃ | የቪዲዮ አጋዥ ስልጠና |
|---|---|---|---|
| The Operators Mitigation (የኦፕሬተሮች የማስተካከያ እርምጃ) ቅደም ተከተል ቻርት በ STREAM™ መሳሪያ ውስጥ ለሚፈጠሩ የተለመዱ የስህተት ኮዶች መፍትሔ ለመፈለግ የተነደፈ ነው። STREAM™ ን ይመልከቱ ለተጨማሪ ማብራሪያ የአሰራር ሂደቶች እና የጥገና መመሪያ መሰረታዊ የማስተካከያ እርምጃዎች ችግሩን ካልፈቱት እና ችግሩ ከቀጠለ በአካባቢዎ የሚገኝ ባለሙያን ያማክሩ ወይም Aqua Research Tech Support (አኳ የጥናት ምርምር የቴክ ድጋፍን) በ-505.414.3929 ያግኙ። | | | |
| ብርት ጥፍት የሚል ቢጫ መብራት | A. ዝቅተኛ የኃይል አቅርቦት<br> | A.1. የኃይል አቅርቦቱን ይፈትሹ። የኃይል አቅርቦቱ ተሰክቷል? ግድግዳው ላይ የኃይል አቅርቦት አለ? ከባትሪ ጋር የተገናኘ ከሆነ ባትሪው ሞቷል ወይስ አነስተኛ ኃይል ነው ያለው?<br>A.2. አሁን ላይ ከተገናኘው የኃይል አቅርቦት ያላቅቁ።<br>A.3. ሌላ የግድግዳ የኃይል ማገናኛ ላይ ይሰኩ ወይም ከተለዋጭ የኃይል ምንጭ ጋር ያገናኙ (ማለትም የመኪና ባትሪ ወይም የፀሐይ ፓነል ኢንቨርተር)።<br>A.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| ደማቅ ቢጫ መብራት | B. ዝቅተኛ የኃይል አቅርቦት<br> | B.1. የኃይል አቅርቦቱን ይፈትሹ። ከግድግዳው ሶኬት፣ ከመኪና ባትሪ ወይም ከፀሃይ ፓነል ክፍል ኃይል አለ?<br>B.2. የ STREAM™ መሳሪያውን ያጥፉ።<br>B.3. ከሌላ የኃይል ምንጭ፣ የግድግዳ ሶኬት፣ ከመኪና ባትሪ ወይም ከፀሃይ ፓነል ኢንቬንተር ጋር ያገናኙ።<br>B.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | C. የጨው መጠኑ በጣም ከፍተኛ ነው<br> | C.1. የጨው ክምችት መጠኑ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። የጨው መጠኑን ለመቀነስ ሙሙቱ ውስጥ ውሃ ይጨምሩ።<br>C.2. የጨው ሙሙቱ በደንብ መቀላቀሉን ያረጋግጡ (ሁሉም ጨው መሟሟቱን) እና የ STREAM™ መሳሪያውን እንደገና ያስጀምሩ።<br>C.3. ስህተትን የሚያመለክት ደማቅ ቢጫ መብራት እስኪበራ ድረስ መሳሪያው እንዲሰራ ያድርጉ።<br>C.4. የቆየውን የጨው ሙመሙት ለማስወጣት መሳሪያውን አጥፍተው ድጋሚ በማብራት እርምጃ C.3 ከ3 እስከ 4 ጊዜ ይድገሙት። | |
| ብርት ጥፍት የሚል ቀይ/ቢጫ/ቀይ መብራት | D. የኃይል አቅርቦት ከክልል ውጪ ነው<br> | D.1. የ STREAM™ መሳሪያውን ያጥፉ።<br>D.2. መሳሪያውን ከኃይል አቅርቦት፣ ከግድግዳ ሶኬት፣ ከመኪና ባትሪ፣ ወይም ከፀሃይ ኢንቨርተር ያላቅቁ።<br>D.3. የ STREAM መሳሪያውን ከሌላ፣ ከተሞከረ የኃይል አቅርቦት ጋር ያገናኙ።<br>D.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| ብርት ጥፍት የሚል ቀይ መብራት | E. የጨው ሙመሙት ማጠራቀሚያው ባዶ ነው።<br> | E.1. መሳሪያው ውስጥ ያለው የጨው ሙመሙት አለማለቁን ያረጋግጡ።<br>E.2. አዲስ የጨው ሙመሙት ያዘጋጁ።<br>E.3. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | F. የጨው መጠኑ በጣም ከፍተኛ ነው<br> | F.1. የጨው ክምችት መጠኑ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። የጨው መጠኑን ለመቀነስ ሙሙቱ ውስጥ ውሃ ይጨምሩ።<br>F.2. የጨው ሙሙቱ በደንብ መቀላቀሉን ያረጋግጡ (ሁሉም ጨው መሟሟቱን) እና የ STREAM™ መሳሪያውን እንደገና ያስጀምሩ።<br>F.3. ስህተትን የሚያመለክት ደማቅ ቀይ መብራት እስኪበራ ድረስ መሳሪያው እንዲሰራ ያድርጉ።<br>F.4. የቆየውን የጨው ሙመሙት ለማስወጣት መሳሪያውን አጥፍተው ድጋሚ በማብራት እርምጃ F.3 ከ3 እስከ 4 ጊዜ ይድገሙት። | |
| | G. የጨው ሙሙቱ ሙቀት ከፍተኛ ነው<br> | G.1. የጨው ሙሙቱ በጣም ሞቃት አለመሆኑን ያረጋግጡ። የሚመከረው የጨው ሙመሙት ሙቀት 50-100°F (10-38°ሴ) ነው<br>G.2. ቀዝቃዛ ውሃ በመጠቀም አዲስ የጨው ሙመሙት ያዘጋጁ።<br>G.3. መሳሪያውን ያብሩ። | |

| የችግር ምልክቶች | መንስኤ | የኦፕሬተር የማስተካከያ እርምጃ | የቪዲዮ አጋዥ ስልጠና |
|---|---|---|---|
|  ያለሟቋረጥ ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ መብራት | H. የግፊት መከላከያው ዲስክ ተሰብሯል። | H.1. የግፊት መከላከያው ዲስክ ያልተሰበረ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>H.2. የተቀደደ ከሆነ የግፊት መከላከያውን ዲስክ ይተኩ።<br>H.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ | |
| | I. የተዘጉ ቱቦዎች ወይም ክፍል | I.1. በመሳሪያው ውስጥ፣ ወደ ፓምፑ፣ በመሳሪያው ክፍል እና ወደ ኦክሳይድ ታንክ ውስጥ የጨው ሙመቱ እያለፈ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>I.2. የቱቦዎቹን መገጣጠሚያዎች እና ቱቦዎች አለመደፈናቸውን ይፈትሹ።<br>I.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ | |
|  ደማቅ ቀይ መብራት | J. የሙመቱ የጨው መጠን በጣም ዝቅተኛ ነው  | J.1. በጨው ሙመሙት ማጠራቀሚያ ውስጥ ያለው ጨው በሙሉ መሟሟቱን ያረጋግጡ።<br>J.2. በፊት የነበረው ጨው ሙሉ በሙሉ የሟሟ ከሆነ፣ ወደ ሙመቱ ጨው ይጨምሩ።<br>J.3. ሙመቱን በደንብ በመቀላቀል ጨው እንዲሟሟ ያድርጉ።<br>J.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | K. የጨው ሙመሙት ማጠራቀሚያው ባዶ ነው  | K.1. መሳሪያው ውስጥ ያለው የጨው ሙመሙት አለማለቁን ያረጋግጡ።<br>K.2. አዲስ የጨው ሙመሙት ያዘጋጁ።<br>K.3. መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | L. የግፊት መከላከያው ዲስክ ተሰብሯል። | L.1. የግፊት መከላከያው ዲስክ ያልተሰበረ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>L.2. የተቀደደ ከሆነ የግፊት መከላከያውን ዲስክ ይተኩ።<br>L.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ | |
| | M. የተዘጉ ቱቦዎች ወይም ክፍል | M.1. በመሳሪያው ውስጥ፣ ወደ ፓምፑ፣ በመሳሪያው ክፍል እና ወደ ኦክሳይድ ታንክ ውስጥ የጨው ሙመቱ እያለፈ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>M.2. የቱቦዎቹን መገጣጠሚያዎች እና ቱቦዎች አለመደፈናቸውን ይፈትሹ።<br>M.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ<br>M.4. መሳሪያውን ያብሩ። | |
|  ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ/አረንጓዴ/ቀይ | N. መሳሪያው ከመጠን በላይ ሞቋል  | N.1. በመሳሪያው ውስጥ፣ ወደ ፓምፑ፣ በመሳሪያው ክፍል እና ወደ ኦክሳይድ ታንክ ውስጥ የጨው ሙመቱ እያለፈ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>N.2. የቱቦዎቹን መገጣጠሚያዎች እና ቱቦዎች አለመደፈናቸውን ይፈትሹ።<br>N.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ | |
| | O. የጨው ሙመቱ ማጠራቀሚያ ባዶ ነው  | O.1. መሳሪያው ውስጥ ያለው የጨው ሙመሙት አለማለቁን ያረጋግጡ።<br>O.2. አዲስ የጨው ሙመሙት ያዘጋጁ።<br>O.3. መሳሪያውን ያብሩ። | |

| የችግር ምልክቶች | መንስኤ | የኦፕሬተር የማስተካከያ እርምጃ | የቪዲዮ አጋዥ ስልጠና |
|---|---|---|---|
| ፓምፑ አይሰራም- ወይም ፍጥነት የለውም | P. የተዘጉ ቱቦዎች፣ መገጣጠሚያዎች ወይም ዝቃጭ የተጠራቀመበት ክፍል | P.1. በመሳሪያው ውስጥ፣ ወደ ፓምፑ፣ በመሳሪያው ክፍል እና ወደ አክሳይድ ታንክ ውስጥ የጨው ሙሙቱ እያለፈ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>P.2. የቱቦዎቹን መገጣጠሚያዎች እና ቱቦዎች አለመደፈናቸውን ይፈትሹ።<br>P.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ<br>P.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | Q. በፓምፕ መጋጠሚያ ውስጥ ቆሻሻ | Q.1. ከፓምፑ መጋጠሚያ ላይ የመጫመቂያ ቱቦዎቹን በማላቀቅ ቆሻሻ ያለመኖሩን ያረጋግጡ።<br>Q.2. ንጹህ ውሃ የመጫመቂያ ቱቦው ውስጥ ያስገቡ።<br>Q.3. የፓምፑን የመጫመቂያ ቱቦ በፓምፑ ራስ ላይ መልሰው በመግጠም ሰማያዊውን ክዳን በታው ይመልሱት።<br>Q.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | R. ፓምፑ ይበራል፣ ነገር ግን ጥርሶቹ አይሽከረከሩም፣ ፓምፑ ይጮሃል | R.1. ከፓምፑ መጋጠሚያ ላይ የመጫመቂያ ቱቦውን ያላቅቁ<br>R.2. የመጫመቂያ ቱቦውን ደጋግመው ይዘርጉ (ይወጥሩ)<br>R.3. የመጫመቂያ ቱቦውን ከፓምፑ መጋጠሚያ (ራስ) ካላቀቁ በኋላ ፓምፑ ያለ ቱቦው የሚሽከረከር መሆኑን ለማየት የ STREAM™ ስርዓቱን ያብሩት። ፓምፑ ያለ ቱቦዎቹ የማይሽከረከር ከሆነ፣ ባለሙያ ያማክሩ።<br>R.4. ፓምፑ እየሰራ ከሆነ ሰማያዊውን የፓምፕ ክዳን መልሰው በመክደን የፓምፑን የመጫመቂያ ቱቦ መልሰው ይግጠሙ።<br>R.5. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | S. የተቀደደ የግፊት መከላከያ ዲስክ | S.1. የግፊት መከላከያው ዲስክ ያልተሰበረ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>S.2. የተቀደደ ከሆነ የግፊት መከላከያውን ዲስክ ይተኩ።<br>S.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ<br>S.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| በ STREAM መያዣ ውስጥ እርጥበት | T. የላሉ መገጣጠሚያዎች፣ በመያዣ ውስጥ እርጥበት። | T.1. የፍሳሹን መነሻ የቱ ጋር እንደሆነ ይመርምሩ።<br>T.2. መሳሪያውን ያጥፉት።<br>T.3. ቱቦዎቹን ይጠግኑ ወይም መገጣጠሚያዎቹን ያጥብቁ።<br>T.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| በመሳሪያው ውስጥ ምንም ፍሰት የለም | U. የተዘጉ ቱቦዎች፣ መገጣጠሚያዎች ወይም ዝቃጭ የተጠራቀመበት ክፍል | U.1. በመሳሪያው ውስጥ፣ ወደ ፓምፑ፣ በመሳሪያው ክፍል እና ወደ አክሳይድ ታንክ ውስጥ የጨው ሙሙቱ እያለፈ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>U.2. የቱቦዎቹን መገጣጠሚያዎች እና ቱቦዎች አለመደፈናቸውን ይፈትሹ።<br>U.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ<br>U.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | V.የግፊት መከላከያው ዲስክ ተሰብሯል። | V.1. የግፊት መከላከያው ዲስክ ያልተሰበረ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>V.2. የተቀደደ ከሆነ የግፊት መከላከያውን ዲስክ ይተኩ።<br>V.3. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ፣ በመመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ<br>V.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | W. በማጥለያው እና በቱቦዎቹ ወይም መገጣጠሚያ መካከል የተላቀቀ ቦታ። | W.1. አይዝጌ ማያያዣው ላይ የጨው ሙሙቱ ማጥለያ ከ ወደ ውስጥ ማሳለፊያ ቱቦው ጋር በትክክል መግጠሙን ያረጋግጡ።<br>W.2. ሁሉንም መገጣጠሚያዎች ያጥብቁ።<br>W.3. ማጥለያው የጨው ሙሙቱ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መጥለቁን ያረጋግጡ። | |

| የችግር ምልክቶች | መንስኤ | የኦፕሬተር የማስተካከያ እርምጃ | የቪዲዮ አጋዥ ስልጠና |
|---|---|---|---|
| ዝቅተኛ የክሎሪን ምርት | X. የጨው መጠን በጣም ዝቅተኛ ነው<br> | X.1. በጨው ሙመሙት ማጠራቀሚያ ውስጥ ያለው ጨው በሙሉ መሟሟቱን ያረጋግጡ። የሚፈለገው የጨው ክምችት 15 ግራም/ሊትር ነው።<br>X.2. በፊት የነበረው ጨው ሙሉ በሙሉ የሟሟ ከሆነ፣ ወደ ሙመቱ ጨው ይጨምሩ።<br>X.3. ሙመቱን በደንብ በመቀላቀል ጨው እንዲሟሟ ያድርጉ።<br>X.4. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | Y. የኃይል አቅርቦት መቋረጥ | Y.1. የ STREAM™ መሳሪያው የኃይል አቅርቦት አለመቋረጡን ያረጋግጡ።<br>Y.2. የኃይል አቅርቦቱን ይፈትሹ። የኃይል አቅርቦቱ ተሰክቷል? ግድግዳው ላይ የኃይል አቅርቦት አለ? ከባትሪ ጋር የተገናኘ ከሆነ ባትሪው ሞቷል ወይስ አነስተኛ ኃይል ነው ያለው?<br>Y.3. አሁን ላይ ከተገናኘው የኃይል አቅርቦት ያላቅቁ።<br>Y.4. ሌላ የግድግዳ የኃይል ማገናኛ ላይ ይሰኩ ወይም ከተለዋጭ የኃይል ምንጭ ጋር ያገናኙ (ማለትም የመኪና ባትሪ ወይም የፀሐይ ፓነል ኢንቨርተር)።<br>Y.5. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | Z. የካልሲየም ካርቦኔት መጠራቀም | Z.1. የቆሸሸ መሳሪያ ቁጥጥር የሌለው የኤሌክትሪክ ኃይል በማሳለፍ እሌክትሮዶች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እና ምርት ሊቀንስ ይችላል።<br>Z.2. በመሳሪያው ውስጥ፣ ወደ ፓምፑ፣ በመሳሪያው ክፍል እና ወደ ኦክሳይድ ታንክ ውስጥ የጨው ሙመቱ እያለፈ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>Z.3. የቱቦዎቹን መገጣጠሚያዎች እና ቱቦዎች አለመደፈናቸውን ይፈትሹ።<br>Z.4. የተከማቸ ካርቦኔትን ከቱቦዎች እና መገጣጠሚያዎች ላይ ያስወግዱ።<br>Z.5. መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪአቲክ አሲድ ያጽዱ። መመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ<br>Z.6. የ STREAM™ መሳሪያውን ያብሩ። | |
| | AA. የመሰሪያው የመስራት አቅም ተሟጧል | AA.1. መሳሪያው የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜው ደርሷል።<br>AA.2. የመሳሪያውን amperage ያረጋግጡ፣ 12—21amps መሆን አለበት።<br>AA.3. ከመሳሪያው እየወጣ ያለውን የፍሰት መጠን ያረጋግጡ። ፍሰት 4.2-5.4ሚሊ/ደቂቃ መሆን አለበት<br>AA.4. የክሎሪን ምርቱን ያረጋግጡ፣ በመመሪያው ውስጥ ያለውን አባሪ C የክሎሪን ሙከራ ይመልከቱ<br>AA.5. በመመሪያው ውስጥ ያለውን ክፍል 7.2.3 ይመልከቱ—የኤሌክትሮሊቲክ መሳሪያ መተካት። | |
| የኃይል አቅርቦቱ ኃይል እየሰጠ አይደለም | AB. የኃይል አቅርቦቱ ተበላሽቷል | AB.1. የ STREAM መሳሪያውን ያጥፉ።<br>AB.2. መሳሪያውን ከኃይል አቅርቦት፣ ከግድግዳ ሶኬት፣ ከመኪና ባትሪ፣ ወይም ከፀሃይ ኢንቨርተር ያላቅቁ።<br>AB.3. በኃይል አቅርቦት ማቀፊያው እና በመቆጣጠሪያ ሳጥኑ መካከል ያለው ማገናኛ በትክክል መግጠሙን ያረጋግጡ።<br>AB.4. የኃይል አቅርቦቱ ማቀፊያ በአይን የሚታይ ብልሽት እንደሌለው ያረጋግጡ።<br>AB.5. የ STREAM መሳሪያውን ከሌላ፣ ከተሞከረ የኃይል አቅርቦት ጋር ያገናኙ።<br>AB.6. የ STREAM መሳሪያውን ያብሩ።<br>AB.7. እነዚህ እርምጃዎች ችግሩን ካላስተካከሉ፣ በኃይል መጨናነቅ ምክንያት የኃይል አቅርቦቱ ማቀፊያ ተጎድቶ ሊሆን ይችላል። | |
| በመሳሪያው ውስጥ ምንም ፍሰት የለም | AC. የተዘጉ ቱቦዎች፣ መገጣጠሚያዎች ወይም ዝቃጭ የተጠራቀመበት ክፍል | AC.1. በመሳሪያው ውስጥ፣ ወደ ፓምፑ፣ በመሳሪያው ክፍል እና ወደ ኦክሳይድ ታንክ ውስጥ የጨው ሙመቱ እያለፈ መሆኑን ያረጋግጡ።<br>- ፍሰቱ ያልተቋረጠ ከሆነ [ምንም ዓይነት መደፈን ወይም መንጠባጠብ ከሌለ]፣ መሳሪያውን በኮምጣጤ ወይም ሙሪያቲክ አሲድ ለ 3-5 ዑደቶች ያጽዱ፣ በመመሪያው ውስጥ ክፍል 7.1.6 ይመልከቱ። ይህ ችግሩን ካስተካከለው ወደ እርምጃ AC.4 ይቀጥሉ።<br>- የጨው ሙመቱ በትክክል እየፈሰሰ ካልሆነ ወደ እርምጃ 2 ይቀጥሉ።<br>AC.2. የካልሲየም ክምችቱ አካባቢ የቱ ጋር እንደሆነ ይለዩ [ትቦዎች፣ መገጣጠሚያዎች፣ ወይም የመሳሪያ ክፍል]<br>AC.3. በተቻለ መጠን የዝቃጭ ክምችትን በእጅዎ ያስወግዱ፤ ይህንንም ለማድረግ ቱቦዎችን ማሸት ወይም መበታተን [ትቦዎችን እና መገጣጠሚያዎችን መፍታት] ሊጠበቅብዎ ይችላል።<br>- መሳሪያው መበታተን የሚያስፈልገው ከሆነ ባለሙያ ያነጋግሩ። | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | AC.4. በዚህ ጊዜ የጨው ሙመቱን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋለውን የውሃ ጥንካሬ ለመለካት፣ ከተካተቱት የውሃ ጥንካሬ መለኪያዎች ውስጥ አንዱን ይጠቀሙ እና ውጤቱን ይመዝግቡ።<br>- ከፍተኛ መለኪያዎች ብዙ ጊዜ ማጽዳት አስፈላጊ መሆኑን ሊያመለክቱ ይችላሉ።<br>AC.5. የ STREAM መሳሪያውን ያብሩ። | |